በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር---236553
ቀን- ጥቅምት 30 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካች:-** አቶ ዓለሙ አሸኔ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ አልማዝ አሸኔ 2. ወ/ሮ ልንቴ አሸኔ

3. ወ/ሮ አዳነች አሸኔ 4. ወ/ሮ ታደለች አሸኔ

5. አቶ ዳግም ቀልቻ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የገጠር መሬት ይዞታ ሲሆን የተጀመረው በቦዲቲ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ እንዲሁም እነ ወ/ሮ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ቡላቼ አሸኔ ጣልቃ ገቦች ነበሩ፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 41437 ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት የክስ አቤቱታ ይዘት፡- ሟች አባታቸዉ በህይወት በነበሩበት ወቅት ያፈሯቸዉ ንብረቶች በአመልካች እጅ የሚገኙ በመሆኑ እና የዉርስ ድርሻቸዉን ለማካፈል ፈቃደኛ ስላልሆኑ የድርሻቸዉን እንዲሰጣቸዉ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካችም የቀረበባቸዉን ክስ አስመልክቶ ምላሻቸዉን እንዲያቀርቡ መጥሪያ ቢላክላቸዉም ሊቀርቡ ስላልቻሉ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በሌሉበት በመመልከት መዝገቡን መርምሮ ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የሟች አቶ አሸኔ አደሬ የሆኑት ንብረቶች 12 ጥማድ የእርሻ እና የግጦሽ ሳር መሬት እንዲሁም በ100 ቅጠል ቆርቆሮ የተሰራ መኖሪያ ቤት ከነኩሽናዉ ጋር አመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑ ስተረጋገጠ የአሁን ተጠሪዎች እና በክርክሩ ጣ/ገብ የነበሩት የሟች ልጆች ድርሻቸዉን ተካፍለዉ እንዲወስዱ በማለት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ዉሳኔ ከተሰጠ በኂላ የአሁን አመልካች የከሳሽ ክስ ሳይደርሰኝ፤ መልስ ሳልሰጥ እንዲሁም ከሳሾች ያቀረቡትን ክስ ለመቀበል እምቢተኛ ስለመሆኤ በምኖርበት ቀበሌ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በሌለሁበት የተሰጠ ዉሳኔ በመሆኑ ዉሳኔዉ እንዲነሳልኝ በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78/1 መሠረት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም መዝገቡን በመመርመር ተከሳሽ የከሳሾች ክስ መጥሪያ ስለመድረሱ በቀን 22/05/2013 ዓ/ም በቀረበዉ መግለጫ ላይ ራሳቸዉ ፈርመዉ ስለመቀበላቸዉ የሚያረጋግጥ ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ያቀረቡት አቤቱታ አግባብነት የለዉም በማለት የቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ በቀን 22/02/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በተሰጠዉ ትዕዛዝ ላይ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታቸዉን ለወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዉ ፍ/ቤቱም በቀን 18/04/2014 ዓ/ም በዋለዉ ችሎት የስር ፍ/ቤት በራሱ የአሁን አመልካችን አቤቱታ ተቀብሎ የአሁን መ/ሰጪዎች ምላሽ እንዲሰጡበት ሳያደርግ እና በተገቢዉ መንገድ ሳያጣራ፤ ከሙጉት አመራር ስርዓት ዉጪ ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ የአሁን አመልካች በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳ በማለት ላቀረበዉ አቤቱታ የአሁን ተጠሪዎችን ምላሽ በመቀበል ተገቢ የሆነ ማጣራት በማድረግ የመሰለዉን ትእዛዝ ይስጥበት ዘንድ መዝገቡን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343 መሰረት ወደ ስር ስር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

በዚሁ መሰረት የቦዲቲ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ጉዳዩን አጣርቶና መርምሮ የአሁን አመልካች የክስ መጥሪያ በቀን 22/05/2013 ዓ/ም ፈርመዉ ስለ መቀበላቸዉ የሚያረጋግጥ መግለጫ ከመዝገቡ ጋራ ተያይዞ ያለ በመሆኑ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታቸዉን ለወላይታ ዞን

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዉ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ የሚነቀፍ ስላልሆነ ይግባኙ አያስቀርብም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ አመልካች የስር ፍ/ቤትን ገለልተኝነት ጥያቄ ዉስጥ አስገብተዉ ክስ ይዛወርልኝ የሚል አቤቱታ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዉ ዉድቅ የተደረገበት መሆኑን፤ ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ/ም የዉርሱን ንብረት እንዲያጣሩ ወደ እርሱ ጋር የሄዱት ዉርስ አጣሪዎች ሲጠይቁት መጥሪያ ያልደረሰዉ መሆኑን የገለጸላቸዉ መሆኑ እንዲሁም አመልካች በችሎት ቀርቦ መጥሪያ የደረሰዉ መሆኑን አምኖ የክስ አልመሰለኝም ያለዉ ሲታይ ለመከራከር ያልፈለገ መሆኑን መረዳት ይቻላል በማለት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ/ትእዛዝ/ በማጽናት ዉስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታዉም ሊቀርብ የቻለዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ ትቶ ወይም ለድርድር ጉዳዩን ከሰጠ በኋላ የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78/1 መሠረት ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገበትን አግባብነት ለማጣራት የሚል ጭብጥ ከያዘና ግራቀኙም መልስ እንዲለዋወጡ ከተደረግን በኋላ በተያዘዉ ጭብጥ መሰረት ተገቢዉን ማጣራት በማድረግ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ የተያዘዉን ጭብጥ ወደ ጎን ትቶ ግራ ቀኛችን መልስ ባልተለዋወጥንበት፤ ጭብጥ ባልተያዘበት ጉዳይ ላይ ዉሳኔ በመስጠት የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ እንዲጸና በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ተገቢ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳ እና ወደ ክርክር እንድገባ ያቀረብኩትን ምክንያት ማለትም ለህገወጥ እስራት መዳረጌን በማስረጃ አስደግፌ ያቀረብኩትን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.78 መሰረት ሳይመዝን እና ምክንያቶችን/ማስረጃ/ ሳያዳምጥ በማለፍ በደፈናዉ የመልስ ሰጪዎችን ቃል በመቀበል ብቻ የሰጠዉ ዉሳኔ ሆኖ ሳለ፤ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ መሰረት የስር ፍ/ቤት የክስ መልስ ሳይቀበል እና ግራ ቀኛችን ክርክር ሳናደርግ በቀጥታ የዉርስ አጣሪ ሽማግሌ እንዲመረጥ በማድረግ ወደ ክርክሩ ካስገባኝ በኋላ በሽማግሌዎች ማጣራት ስላልተስማማሁኝ በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲጸና መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ መሰረታዊ የህግ እና የማስረጃ ምዘና ጥሰት የተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ተሽሮ በሌለሁበት የተሰጠዉ ዉሳኔ ተነስቶ ወደ ክርክሩ ገብቼ ክርክሬን እንዳሰማ እንዲወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት አጣርቶ ወስኗል ወይ? እንዲሁም ከአጠቃላይ የክርክር አመራር ሥርዓት አንጻር ተገቢነቱን ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች የክስ ቻርጅና የፍ/ቤት መጥሪያ ደርሶት ፈርሞ ከተቀበለ በኋላ ለተከሰሱበት ጉዳይ መልስ ለመስጠትም ሆነ ህግን አክብሮ ችሎት መቅረብ ባለመፈለጋቸዉ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉን መሰረት ያደረገ እና ምንም አይነት ስህተት ያለበት አይደለም፡፡ የወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥና እንዲከራከር ቢፈቅድም በድጋሚ መብቱን መጠቀም ባለመፈለግ ባሳለፈበት ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ በመተቸት ያቀረበዉ አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 90452 እና 10147 ከሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንጻር ተቀባይነት የሌለዉ ነዉ፡፡ አመልካች መልስ እንዲሰጥና እንዲቀርብ በተያዘለት ቀጠሮ ችሎት የቀረበ ቢሆንም ለቀረበበት ክስ መልስ ሳይይዝ የቀረበ እና ለማቅረብ ያልቻለበትን ምክንያት ሳይገልጽ እንዲሁም መልስ ለማቅረብ የሚፈልግ መሆኑን ባልገለጸበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት የከሳሾችን (የአሁን ተጠሪዎችን) ክስ፣ ክርክርና የአጣሪ መግለጫ መነሻ አድርጎ ተገቢዉን ዉሳኔ መስጠቱ ሚዛናዊ እና ሥነ ሥርዓታዊ ሊባል የሚችል ነዉ፡፡ አመልካች እያደረገ ያለዉ ክርክር ከቅን ልቦና ዉጭ ሆነ ብሎ በሀሰት ተጠሪዎችን ለመጉዳት በማሰብ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ አመልካች ባቀረበዉ አቤቱታ መሰረት መልስ የማቅረብ መብቱ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተጠብቆለት መዝገቡ ወደ ሥር ፍ/ቤት ከተመለሰ በኃላም በድጋሚ ለክሱ መልስ ለመስጠትም ሆነ ችሎት ለመቅረብ ባለመፈለግ ካለአሳማኝ ምክንያት መብቱን አሳልፎ ባለበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ዉሳኔ በመመርመር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 70/ሀ/፣ 78/1/ እና 295 እና 196 ድንጋጌዎችና ዓላማ ዉጭ መሆኑን አረጋግጦ ዉሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ ስህተት ሊባል የሚችል ስላልሆነ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንዲጸና በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ መርምረን እንደተረዳነዉ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻዉ ነጥብ የስር ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚዉ ፍ/ቤት በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት አጣርቶ ወስኗል ወይ? እንዲሁም አመልካች በሌሉበት እንዲታይ የተሰጠዉ ትዕዛዝ ሆነ ዉሳኔ ተነስቶ ባለበት እንዲታይ ያቀረቡት አቤቱታ ዉድቅ መደረጉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78 ድንጋጌ አንጻር ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነዉ፡፡

በመሠረቱ አንድ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ወይም ዉሳኔ የተሰጠበት ወገን ጉዳዩ ባለበት እንዲታይ አቤቱታዉን ማቅረብ ያለበት ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ መሰጠቱን ወይም በጉዳዩ ላይ ዉሳኔ መሰጠቱን በተረዳዉ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ መሆኑን እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78(1) ድንጋጌ የሚያሳይ ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 ደግሞ ተከሳሹ ይህን ማመልከቻ በሚያቀርብበት ጊዜ የመጥሪያዉ ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰዉ መሆኑን ወይም ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀርቦ መከራከሪያዉን ያላሰማዉ ወይም መልስ ያልሰጠዉ በበቂ ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ የተረዳ እንደሆነ የተከሳሹ አቤቱታ ላንደኛዉ ወገን ተከራካሪ እንዲደርሰዉ ካደረገና ተገቢዉን ኪሳራ ወይም መቀጮ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንዲከፍል ካዘዘ በኃላ ትዕዛዙን ወይም ብይኑን በማንሳት ክርክሩ እንደገና የሚሰማበትን ቀን ቀጠሮ ይሰጣል በማለት ደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉ ማመልከቻዉ ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለዉ በቅድሚያ ትዕዛዙ ወይም ዉሳኔዉ መሰጠቱን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ማመልከቻዉ የቀረበ መሆን ያለበት ሲሆን ሌላዉ ደግሞ መጥሪያዉ በአግባቡ ያልደረሰዉ መሆኑን ወይም ክርክሩን ወይም መልሱን ያላቀረበዉ በበቂ ምክንያት መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም መጥሪያ ፈርሞ ተቀብሎ የክስ አልመሰለኝም ወይም ክርክር መኖሩን እያወቀ ሳይቀርብ ቀርቶ መጥሪያ በአግባቡ አልደረሰኝም በማለት የሚያቀርበዉ ምክንያት በቂ ነዉ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አይሆንም፡፡ እነዚህ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት የቀረበ ማመልከቻ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካች አቤቱታ ለተጠሪዎች እንዲደርሳቸዉና አስተያየታቸዉን ተቀብሎና አጣርቶ እንዲወስን ለወረዳዉ ፍ/ቤት በመለሰዉ አግባብ ተጠሪዎች የካቲት 15 ቀን 2014 ዓ.ም የተዘጋጀ አስተያየት እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡ ተጠሪዎችም አመልካች መጥሪያ ፈርሞ ተቀብሎ ሲያበቃ መጥሪያ አልደረሰኝም የሚሉት በሀሰት ሊያጉላላቸዉ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ምንም እንኳ መጥሪያ ያልደረሳቸዉ መሆኑን ገለልጸዉ ቢከራከሩም፤ ራሳቸዉ ጥር 22 ቀን 2013 ዓ.ም አስቀድሞ ባቀረቡት መግለጫ መጥሪያ ፈርመው ቀበሉን ካረጋገጠ በኃላ መልሶ በቃል ክርክር ወቅት ክስ መሆኑን ሳያዉቅ ፈርሞ እንደተቀበለ በመግለጽ የሚያቀርበዉ ክርክር ተገቢነት የለዉም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ አድርጓል፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገዉ መጥሪያ የደረሰዉ መሆኑንና ክርክር መኖሩን እያወቀ ዉጤቱን ጠብቆ ያቀረበዉ መሆኑን በማረጋገጥ አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረጉ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ አመልካች በወቅቱ እስራ ላይ በመቆየታቸዉ ቀርበዉ ሊከራከሩ እንዳልቻሉ በዚህ ሰበር ደረጃ ያቀረቡት በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተገቢነት የለዉም፡፡

ከላይ ከተገለጸዉ በተጨማሪ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤትን መዝገብ አስቀርቦ ማረጋገጥ እንደቻለዉ አመልካች የስር ፍ/ቤት ገለልተኛ እንዳልሆነ በመግለጽ ችሎት እንዲዛወርላቸዉ ለወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበዉ በመ/ቁ 54234 የካቲት 02 ቀን 2013 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ አቤቱታቸዉ ዉድቅ ከመደረጉም በላይ ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም ወደ አመልካች የተላኩት ዉርስ አጣሪዎች አመልካችን ሲጠይቁት መጥሪያ እንዳልደረሰዉ መግለጹ ሲታይ አመልካች ክርክር መኖሩን እያወቀ ቀርቦ እንዳልተከራከረ ያረጋግጣል በማለት የስር ፍ/ቤትን ብይን አጽንቷል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ አመልካች የደረሰዉ መጥሪያ የክስ መሆኑን አልተረዳም ቢባል እንኳ ክርክር መኖሩን እያወቀ ለመከራካር እንዲፈቀድለት ሳይጠይቅ ቆይቶ የፍርዱን ዉጤት ካወቀና ተረቺ ከሆነ በኃላ ያቀረበዉ አቤቱታ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78 ድንጋጌን አያሟላም ተብሎ የአመልካች አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ዉድቅ መደረጉ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሲጠቃለል በቦዲቲ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተሰጥቶ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ የጸናዉ ዉሳኔ/ብይን/ የሚነቀፍበት በቂ ምክንያት ባለመኖሩ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1) አንጻር ሲታይ ዉሳኔዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት ባለመቻሉ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. በቦዲቲ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ12586 ግንቦት 12 ቀን 2014 ዓ.ም ተሰጥቶ በወላይታ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 55988 ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ41437 ጥቅምት 03 ቀን 2015 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ለ) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በቦዲቲ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14074 የተጀመረዉ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !